# ለቤት እንክብካቤ ረዳቶች የክህሎት ልምምዶች አሠራር ማረጋገጫ ዝርዝር
# DSHS ጸድቋል
## Skills Practice Procedure Checklist for Home Care Aides DSHS Approved

ይህ የክህሎት ልምምድ አሠራር ዝርዝር በቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳቶች የመማሪያ ክህሎቶች በሥራ ላይ ባሉ የሥልጠና መርሃግብሮች ወይም የእንክብካቤ ሥርዓት-ትምህርቶች መሠረታዊ ሥርዓቶች ወይም ሌሎች ተቀባይነት ባላቸው የሥልጠና ቁሳቁሶች በመጠቀም በኮሚኒቲ አስተማሪዎች የሚጠቀሙበት ነው፡፡ ለክዕሎቱ አስተማማኝ አፈፃፀም ወሳኝ የሆኑ ደረጃዎችን በዚህ የአሠራር መመሪያ ውስጥ ደማቅ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ተግባራት የፕሪሜትሪክ ፈተና አካል አይደሉም ፣ ሆኖም ግን ፣ የዕለት ተዕለት ኑሮን እንቅስቃሴ የሚደግፉ እነዚህ ሁሉ ተግባራት እንደ ማንኛውም የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት የምስክር ወረቀት ክፍል አካል ብቃት ያለው አስተማሪ ባሉበት እንዲታዩ ያስፈልጋል፡፡ አስደሳች እና ደስተኛ ሥልጠና ይኑርዎት!

## የርዕስ ማውጫ የገጽ ቁጥር


የጋራ እንክብካቤ ልምዶች ........ 1
የግንኙነት እና የደንበኛ መብቶች ........ 1
S.W.I.P.E.S ........ 1
እጅን መታጠብ ........ 1
ጓንት ያድርጉ ........ 2
ጓንት ይውሰዱ ........ 2
የግል መከላከያ መሣሪያዎችን (PPE) ይጠቀሙ ........ 2
ደንበኛው እንዲራመድ ይርዱ ........ 2
ደንበኛ ከአልጋ ወደ ወንበር ወይም በተሽከርካሪ ወንበር ያስተላልፉ ........ 2 / 3
ደንበኛን በአልጋ ላይ ማዞር እና ማስቀመጥ ........ 3
የአፍ / ኦራል እንክብካቤ ........ 4
ሰው-ሰራሽ ጥርስ ማጽዳትና ማስቀመጥ ........ 4
የጣት ጥፍር እንክብካቤ ........ 4 / 5
የእግር እንክብካቤ ........ 5
ለጥፍር እንክብካቤ አጠቃላይ ምክሮች ........ 6
ደንበኛን ለመልበስ በማይሰራ ክንድ ይርዱ ........ 6
ጉልበት ጋር የሚደርስ ካልሲ ደንበኛ ላይ ማድረግ ........ 6
ለአንድ ትከሻ የቀስታ እንቅስቃሴ (ROM) ........ 6 / 7
የቀስታ እንቅስቃሴ ROM ለአንድ ጉልበት እና ለቁርጭምጭሚት ........ 7
ደንበኛ እንዲበላ ይረዱ ........ 7
ደንበኛን በአልጋ ላይ ጽዳት መርዳት ........ 7 / 8
በብልት እንክብካቤ እገዛ ........ 8
የካቴተር እንክብካቤ ........ 9
የኮንዶም ካቴተር ክብካቤ (በመጠባበቅ ላይ ያለ ግምገማ ፣ የሚመለከተው ከሆነ ማሳየት) ........ 9
የመድኃኒት ድጋፍ ........ 10
የአልጋ ላይ ፖፖ በመጠቀም ደንበኛን ያግዙት ........ 10
በደህንነት ምላጭ መላጨት ........ 10


**የማጠናቀቂያ ማረጋገጫ፡**ለእያንዳንዱ የ*OJT* ክህሎቶችን ስልጠና ላጠናቀቀ ተማሪ ይህ ገጽ በ ALF, AFH, ወይም ESFላይ ለ TrainingApprovalTPA@dshs.wa.gov መላክ ***አለበት*** ፡፡........ 11

<u>እባክዎን የሚከተለው ያስተውሉ፡</u> ሁሉም የክህሎት ተግባራት በተፈቀደለት አስተማሪ መማር እና በቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት እጩ ማሳየት አለባቸው፡፡ የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት ክህሎቶች አፈፃፀም በአካላዊ ትክክለኛ አሻንጉሊት በመጠቀም ሊገመገም ይችላል፡፡

<u>ተጨማሪ መረጃዎች፡</u>
<u>የፕሮሜትሪክ (Prometric) የቤት እንክብካቤ ረዳት የማረጋገጫ ዝርዝር</u>
የ <u>Washington ግዛት የጤና መምሪያ የቤት እንክብካቤ ረዳት ምርመራ ዝግጅት መጽሀፎች</u>

Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

# ለቤት እንክብካቤ ረዳቶች የክህሎት ልምምዶች አሠራር ማረጋገጫ ዝርዝር
# በ DSHS የጸደቀ
## Skills Practice Procedure Checklist for Home Care Aides DSHS Approved

| **የተለመዱ የሕክምና ልምዶች - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡** | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| እንክብካቤ ሲጀምሩ እራስዎን ለደንበኛው ያስተዋውቁ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን እና እራስዎን በአሰራሩ ለመጠበቅ የኢንፌክሽን መቆጣጠሪያ እርምጃዎችን እና መደበኛ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| በሂደቶች ሁሉ ውስጥ የደንበኛውን ማህበራዊ እና ሰብአዊ ፍላጎቶችን ያስተዋውቁ | ☐ | ☐ |
| በሁሉም ሂደቶች ውስጥ የደንበኛውን **መብቶች** ያስተዋውቁ | ☐ | ☐ |
| በሁሉም ሂደቶች ውስጥ የደንበኛውን **ደህንነት** ያስተዋውቁ | ☐ | ☐ |
| በሁሉም ሂደቶች ውስጥ የደንበኛውን **ምቾት** ያስተዋውቁ | ☐ | ☐ |
| በእንክብካቤ መጨረሻ ላይ በተደጋጋሚ መጠቀሚያ ዕቃዎችን በደንበኛው ተደራሽነት ውስጥ ይተው ለምሳሌ ስልክ ፣ መነጽሮች ፣ ሪሞት ፣ ሶፍት ፣ ውሃ በብርጭቆ) | ☐ | ☐ |

| **የግንኙነት እና የደንበኛ መብቶች - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡** | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| ምን እንደምታደርግ ማብራራ | ☐ | ☐ |
| በቀስታ ፣ በግልፅ እና በአክብሮት ይናገሩ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛን ያሳትፉ እና በትኩረት ያዳምጡ | ☐ | ☐ |
| ለለውጦች ደንበኛውን ይመልከቱ | ☐ | ☐ |
| የደንበኞችን ምርጫ እና ነፃነት ይደግፉ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛን የግላዊነት ፍላጎት ያክብሩ | ☐ | ☐ |

| **S.W.I.P.E.S. - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡** | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| ሥራ ከመጀመሩ በፊት **አቅርቦቶችን** ይሰብስቡ | ☐ | ☐ |
| ከደንበኛዎ ጋር ከመገናኘትዎ በፊት እጅዎን **ይታጠቡ** | ☐ | ☐ |
| ለደንበኛው ስምዎን በመናገር እራስዎን **ያሳውቁ** | ☐ | ☐ |
| በመጋረጃ ፣ ስክሪን ወይም በበር በመሸፈን ግላዊነትን **ይጠብቁ** | ☐ | ☐ |
| ለደንበኛው ምን እንደሚያደርጉ **ያብራሩ** | ☐ | ☐ |
| ተግባሩ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁሉም ነገር ወደ ቦታው እንደተመለሰ እርግጠኛ ለመሆን አካባቢውን **ይቃኙ** | ☐ | ☐ |

| **እጅ መታጠብ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡** | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| ምንም የተበከለ ቦታ እምንዳይነካ አቅርቦቱ በቀላሉ ሊደረስበት የሚችል መሆኑን ያረጋግጡ በሁሉም ተግባራት ላይ | ☐ | ☐ |
| በመታጠቢያ ገንዳ ላይ ሞቅ ያለ ውሃ ያብሩ | ☐ | ☐ |
| **እጆች እና አንጓዎች በደንብ ያርሱ** | ☐ | ☐ |
| ለእጆች ሳሙና ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| **የጣቶችን እና የእጆችን ሁሉንም ገጽታዎች ከእጅ አንጓዎች በላይ ያለውን ጨምሮ ጣቶችን ወደ ታች በማድረግ ቢያንስ ለ20 ሰከንዶች በማሸት አረፋ ያውጡ** | ☐ | ☐ |
| እጆችንና የእጅ አንጓዎችን ሁሉ እጆችን ሳይበክሉ በደንብ ያለ ቅልቁ (ጣቶችን ወደታች በማድረግ) | ☐ | ☐ |
| ሁሉንም ጣቶች፣ እጆች እና የእጅ አንጓዎችን በሙሉ ከጣት ጫፍ በመጀመር ለማድረቅ ንፁህ የወረቀት ፎጣ ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| እጆችን ሳይበክሉ ቧንቧውን ለመዝጋት ንጹህ፣ ደረቅ የወረቀት ፎጣ ወይም ንጹህ፣ ደረቅ የወረቀት ፎጣ አካል ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ቧንቧ ከዘጋ በኋላ ወዲያውኑ የተጠቀሙበትን የወረቀት ፎጣዎችን በቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ ይጣሉ | ☐ | ☐ |
| ብክለትን በማስወገድ በንጹህ እጆች የአሰራር ሂደቱን ያጠናቅቁ (ለምሳሌ ከቧንቧ መዝጊያ፣ የወረቀት ፎጣ መጣያ ፣የእቃ መታጠቢያ ወይም የቆሻሻ መጣያ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት) | ☐ | ☐ |

**ጓንት ማድረግ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ከመያዝዎ በፊት እጅዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |
| ከመጠቀምዎ በፊት እያንዳንዱን ጓንት ቀዳዳ ወይም ሌላ ብልሹ እንዳለው ይፈትሹ | ☐ | ☐ |
| ጓንቱን በጫፉ ይያዙ እና ወደእጅ ያስገቡ | ☐ | ☐ |
| ሌላኛውን ጓንት በጫፉ ይያዙ እና ወደ ሌላኛው እጅ ይጎትቱ | ☐ | ☐ |
| ጓንቶች በእያንዳንዱ ጣት ላይ በትክክል መግባቱን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |

**ጓንት ማውለቅ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| በአንደኛው ጓንት ባደረገ እጅ ፣ ሌላኛውን ጓንት ከውጭ በኩል ጫፉን ይያዙት | ☐ | ☐ |
| ጓንቱን በእጅዎ ላይ ከውስጥ ወደውጭ ይጎትቱ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ባደረገ እጅ የወለቀውን ጓንት ይያዙ እና እንደኳስ ይጨምድዱት | ☐ | ☐ |
| በባዶ እጅ በሁለት ጣቶች የሁለተኛው ጓንት ጫፍ በውስጥ በኩል ይያዙ | ☐ | ☐ |
| የመጀመሪያውን ጓንት እንዲሸፍነው አድርገው ጓንቱን ከውስጥ ወደውጭ ያውልቁ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ያስወግዱ ፣ጓንት በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ይጣሉ እና እጅዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**የግል መከላከያ መሣሪያዎችን (PPE) መቼ እንደሚጠቀሙ ለመለየትና PPEን ለማድረግንና ለማውለቅ የበሽታ መቆጣጠርና መከላከል ማዕከል (CDC) መመሪያዎችን ይከተሉ - የእነዚህን ክዕሎቶች በተሳካ ሁኔታ ለመጨረስ፥ ከክዕሎት አስተማሪዎ ጋር አሁን ያለውን የPPE ፕሮቶኮል ሁሉ መለማመድን ይከተሉ።**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የግል ንፅህና መጠበቂያ መሳሪያ PPE /CDC መጠቀም | ☐ | ☐ |

**ደንበኛ ለመራመድ መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ወደ ደንበኛው በመዞር ከፊት ለፊት ይቁሙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው የማያንሸራትት ጫማ እንዲያደርጉ እና በትክክል እንዲያስሩ ይረዱ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው መራመድ ከመጀመሩ በፊት የጉዞውን መዳረሻ ያስረዱ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን ጉልበት በ 90 ዲግሪ ማእዘን በማድረግ፣ መርገጫ እግሩን ወለሉ ላይ በማድረግ ደንበኛን ለመቆም ያዘጋጁ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ከመቆሙ በፊት ወንበሩ ላይ እንዳለ ወደፊት እንዲጠጋ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በደንበኛ ወገብ ዙሪያ የማሸጋሸሪያ ቀበቶ (አስፈላጊ ከሆነ) ያድርጉ፥ ደንበኛውም እንዲቆም ይርዱ። | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው በክንዱ ወንበሩን በመግፋት እንዲቆም ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| እጅዎን በደንበኛ ክንድ ላይ፥ ወገብ ላይ ያድርጉ ወይም ደንበኛው በሚቆምበት ጊዜ የማሸጋገሪያውን ቀበቶ ይያዙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ከቆመበት በኋላ ወይም እየሄደ ምን እንደሚሰማው ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን ጀርባ በመያዝ ወይም የማሸጋገሪያ ቀበቶ ከተጠቀሙ እሱን አጥብቀው በመያዝ | ☐ | ☐ |
| ደህንነት ተጠብቆ ለመቀመጥ እግሮችን በወንበሩ መቀመጫ መሃል ላይ በማድረግ ደንበኛው ከመቀመጡ በፊት ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ከመቀመጡ በፊት ወንበሩን እንዲያገኘው ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ሲቀመጥ እጅዎን በደንበኛው ክንድ፣ ጀርባ፣ ወገብ ላይ ያኑሩ ወይም ጥቅም ላይ የዋለውን የማሸጋገሪያ ቀበቶ ይያዙ፡፡ የማሸጋገሪያ ቀበቶን ያስወግዱ፡፡ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛው ዳሌዎችን ከወንበሩ ጀርባ ላይ ትክክል በማስቀመጥ ይተዉት | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለኤች.ሲ. የክህሎት ሙከራ፤ ደንበኛው ለመራመድ መደገፊያ ድጋፍ ይፈልጋል፡፡ ድጋፍ ሰጪ መሳሪያዎችን መጠቀም ግን አያስፈልግም። እንክብካቤው በሚጀመርበት ወቅት ደንበኛው ወንበር ላይ ተቀምጠዋል፡፡**

**ደንበኛውን ከአልጋ ወደ ወንበር ወይም ወደ ተሽከርካሪ ወንበር ማዞር - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| የተሽከርካሪ ወንበር እጀታው ከአልጋው ጋር እስኪገናኝ ድረስ ወንበሩን ወይም ተሽከርካሪ ወንበሩን ማስጠጋት | ☐ | ☐ |
| **ተሽከርካሪ ወንበር ላይ ጎማውን መቆለፍ** | ☐ | ☐ |
| የእግር መርገጫዎቹን ማጠፍ ወይም ማስወገድ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ወደ አልጋው ጎን እንዲንከባለል ይረዱ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን የኋላ ትከሻ ወይም ጀርባ እና ዳሌ በመያዝ ደንበኛው እንዲቀመጥ ድጋፍ ይስጡት | ☐ | ☐ |

| ደንበኛውን ከአልጋ ወደ ወንበር ወይም ተሽከርካሪ ወንበር ማዞር - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ (የቀጠለ)፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| ደንበኛን የማያንሸራትት ጫማዎችን እንዲያደርግ ይርዱ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ከመቆሙ በፊት እግሩ በወለሉ ላይ ለጥ ብሎ መቆሙን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| በማሽጋገሪያ ቀበቶ እና በደንበኛው ሰውነት መካከል የተዘረጋ የእጅ ክፍተት ያህል በመተው በደንበኛ ወገብ ዙሪያ፣ ከልብስ በላይ የማሽጋገሪያ ቀበቶውና ማድረግ (አስፈላጊ ከሆነ) | ☐ | ☐ |
| በደንበኛው ፊት ይቁሙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው እንዲቆም እና በአጠቃላይ ሲተላለፍ ሲረዱ በጎን በኩል ወይም ከኋላ ጀርባ የማሽጋገሪያ ቀበቶን ይያዙ | ☐ | ☐ |
| አንድ ወይም ሁለቱን የደንበኛ እግሮች በእራስዎ እግሮች ይደግፉ ፣ ከዚያ ደንበኛው እንዲቆም ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| የእግሮች ጀርባ በተሽከርካሪ ወንበር መቀመጫ መሀላ ላይ እንዲሆን ደንበኛውን በቆመበት ያዙሩት | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው በተሽከርካሪ ወንበር ላይ ከመቀመጡ በፊት እጀታውን እንዲይዝ ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| በተሽከርካሪ ወንበር ላይ በጥንቃቄ እና በቀስታ ዝቅ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛው ዳሌዎች የተሽከርካሪ ወንበርን ጀርባ እንዲነካ በማድረግ ደንበኛውን ያስተካክሉ እንዲሁም የደንበኛው አካል ከወንበር ጋር መጣጣሙን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| የማሽጋገሪያ ቀበቶ ማውለቅ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛን እግር በእግር መርገጫያዎች ላይ ያኑሩ፣ በደንበኛ ምርጫ እና / ወይም ደህንነት የተሽከርካሪ ወንበርን መቆለፍ / አለመቆለፍ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን በተሽከርካሪ ወንበር ላይ በተገቢው የሰውነት አሰላለፍ እና እግሩን በእግር ማረፊያ ላይ በማስቀመጥ ይተዉት | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ እንክብካቤ ደንበኛው በአልጋ ላይ ተኝቶ ይጀምራል፡፡ ደንበኛው መቆም ይችላል ነገር ግን መራመድ አይችልም። የማሽጋገሪያ ቀበቶ በጥቅም ላይ ውሏል፡፡**

| ደንበኛን በአልጋ ላይ አዙረው ያስቀምጡ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች /የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| የአልጋውን ራስጌ ዝቅ ያድርጉ፣ ቀድሞ ዝቅ ካላለ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን ለማዞር ካቀዱት አቅጣጫ በተቃራኒው ከአልጋው ጎን ይቆሙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ወደ እርስዎ እንዲጠጋ ያመቻቹ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ወደ እርስዎ እንዲጠጋ ማድረግ ካልቻሉ ደንበኛውን በጥንቃቄ መገልበጥ እንዲችሉ የደንበኛውን አጠቃላይ አካል በማስተካከል እና ወደ ራስዎ በማስጠጋት ይርዱ | ☐ | ☐ |
| ሁለቱንም እጆች ከደንበኛው ራስ /ትከሻ በታች ያድርጉ እና ያንን የሰውነት ክፍል ወደ እርስዎ ያንቀሳቅሱ | ☐ | ☐ |
| ሁለቱንም እጆች ከደንበኛው ሆድ እና መቀመጫ በታች አድርገው ያንን የሰውነት ክፍል ወደ እርስዎ ያንቀሳቅሱ | ☐ | ☐ |
| ሁለቱንም እጆች ከደንበኛው ጭኖች እና የታችኛው እግሮች አድርገው ያንን የሰውነት ክፍል ወደ እርስዎ ያንቀሳቅሱ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን ለማዞር ያቀዱትን አልጋ ወደ ጎን ይመለሱ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን ክንድ በደረታቸው ላይ በማስቀመጥ ደንበኛውን በሚያዞሩበት አቅጣጫ እግሮቻቸው መጣመራቸውን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| እጆችዎን በደንበኛው ዳሌ እና ትከሻ ላይ ያኑሩ እና ደንበኛውን በቀስታ ወደ እርስዎ ጎን ያዙሩ **(ጠቃሚ ምክር፡ ደንበኛውን ለማዞር የሚያስችል ቦታ እንዳለ ያረጋግጡ)** | ☐ | ☐ |
| **ደንበኛውን ወደ ጎን ሲያዞሩ ከአልጋው ጫፍ አስተማማኝ ርቀት ያስቀሩ** | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን በትክክለኛ የሰውነት አቀማመጥ ላይ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በትራስ የተደገፈ ጭንቅላት | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ክንዱ ላይ እንዳይተኛ እና የላይኛው ክንድ እንዲደገፍ ትከሻ ይስተካከላል፡፡ የደንበኛውን ዝቅተኛ ክንድ እና ትከሻ ከጎን ወደ ታች እንዳይገባ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በመደገፊያ መሣሪያ የተደገፈ ጀርባ የደንበኛን የጎንዮሽ አስተኛኘት ለመጠበቅ መሳሪያውን (ለምሳሌ ስፖንጅ፣ ትራስ) በጀርባ ይደግፉ | ☐ | ☐ |
| የላይኛው ጉልበት ታጥፎ፣ ዳሌ በትክክለኛ ሁኔታ ላይ ሆኖ የላይኛው እግር በመደገፊያ መሣሪያ ተደግፎ፡፡ የላይኛው እግርን ለመደገፍ መሣሪያ (ለምሳሌ ስፖንጅ፣ ትራስ) ይጠቀሙ፣ የላይኛው ዳሌን ያስተካክሉ ፣የላይኛው ጉልበት እንደታጠፈ ይተውት | ☐ | ☐ |
| በዳሌ አጥንት ላይ ቀጥተኛ ግፊትን በማስወገድ ደንበኛውን በጎንዮሽ በማስተኛት ይተውት፡፡ አልቦዎች (ቁርጭምጭሚቶች) እና ጉልበቶች ተለያይተው | ☐ | ☐ |
| የላይኛው ክንድ በሚደግፍ መሣሪያ ይደግፉ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን በላይኛው አንሶላ ይሸፍኑ ፣ ጓንት ያስወግዱ (ከተጠቀሙ) እና እጅዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ እንክብካቤው ደንበኛው በጀርባቸው አልጋ ላይ ተኝው ይጀምራል፡፡**

**የአፍ/ኦራል  እንክብካቤ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ቀጥ ብሎ መቀመጡን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ እና ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የአፍ እንክብካቤ ከመስጠትዎ በፊት በደንበኛው ደረቱ ላይ ፎጣ ለማስቀመጥ ያቅርቡ | ☐ | ☐ |
| ከመጀመርዎ በፊት ስለ ማንኛውም አፍ ህመም ለደንበኛው ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| የጥርስ ብሩሽ ወይም የጥርስ ስፖንጅ ያርሱ እና የጥርስ ሳሙናን ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| ለስላሳ የክብ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም ሁሉንም የጥርስ ገጽታዎችን በብሩሽ ወይም በስፖንጅ ያፅዱ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን ምላስ ለመቦረሽ ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| ደንበኞች አፉቸውን ለማፅዳት ንጹህ ውሃ ያቅርቡ | ☐ | ☐ |
| የተለቀለቀበትን ውሃ ለመቀበል በደንበኛው አገጭ አጠገብ ገንዳውን ይያዙ | ☐ | ☐ |
| የደንበኞቹን ከንፈሮች እና ፊት ማድረቅ እና ፎጣውን ያንሱ | ☐ | ☐ |
| ገንዳውን አለቅልቀው ያድርቁ እና ከማስቀመጥዎ በፊት የጥርስ ብሩሽን ያለቅልቁት | ☐ | ☐ |
| ጓንቶቹን አንስተው ያስወግዱ። እጆችዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ  ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው ጠረጴዛ አጠገብ ይቀመጣል፡፡**

**ሰው-ሰራሽ ጥርስ ማጽዳትና ማስቀመጥ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በማፅዳት ወቅት ሰው-ሰራሽ ጥርስ ከወደቀ የሰው-ሰራሽ ጥርሱን የመሰበር አደጋን ለመቀነስ ዘዴን ይጠቀሙ (ለምሳሌ ሰው-ሰራሽ ጥርስ በቀጥታ ሲንክ ላይ ማጠቢያ ጨርቅ / የወረቀት ፎጣ / ፈጣ በማድረግ፣ ገንዳው ውስጥ ውሀ በመሙላ መቦረሽ) | ☐ | ☐ |
| በሀደቱ በአቃላይ ደንበኛውን ከሰው-ሰራሽ ጥርስ ብክለት ይከልክሉ (ለምሳሌ፣ በስንክ ውሃ ውስጥ መንሳፈፍ ወይም ያልተሸፈነ ቦታ ላይ በቀጥታ የሰው ሰራሽ ጥርስን ማስቀመጥ... | ☐ | ☐ |
| ሰው ሰራሻን ጥርስ ከደንበኛው ይውሰዱ፡፡ ደንበኛው እራሱ ማውጣት ካልቻለ የደንበኛው አፍ ላይ ያለውን ሰው-ሰራሽ ጥርስን በቀስታ ያስወግዱ።  መጀመሪያ የታች ያላውን ሰው-ሰራሽ ጥርስን፣ ከዚያ የላይ ያለውን ሰው-ሰራሽ ጥርስን ያውጡ- | ☐ | ☐ |
| ከመቦረሽዎ በፊት ሰው-ሰራሽ ጥርስን በቀዝቃዛ ፈሳሽ ውሃ ይጠቡ | ☐ | ☐ |
| በጥርስ ብሩሽ ላይ የጥርስ ሳሙና ወይም ሰው-ሰራሽ ጥርስ ማጽጃ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በሁሉም ቦታዎች ላይ ሰው-ሰራሽ ጥርስን ይቦርሹ | ☐ | ☐ |
| ሁሉንም ሰው-ሰራሽ ጥርስ ቦታዎች በቀዝቃዛና በሚፈስ ውሃ ይጠቡ | ☐ | ☐ |
| ሰው-ሰራሽ ጥርስን በመቀየር ወይም በማስቀመጥ ደንበኛን ይርዱ | ☐ | ☐ |
| ሰው-ሰራሽ ጥርስን በውስጡ ከማስገባትዎ በፊት ሰው-ሰራሽ ጥርስ ማስቀመጫውን ይጠቡ | ☐ | ☐ |
| ውህድ ወይም ቀዝቃዛ ውሀ ባለበት ሰው-ሰራሽ ጥርስ ማስቀመጫውን ውስጥ ሰው-ሰራሽ ጥርስን ያስቀምጡ | ☐ | ☐ |
| የሲንክ ማጠቢያ ወይም ሌሎች የቆሸሹ ነገሮችን ያስወግዱ፡፡  ጓንቶችን ያውልቁ እና ያስወግዱ፡፡  እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ  ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው በጠረጴዛ አጠገብ ይቀመጣል  ወይም  በአልጋ ላይ ይተኛል፡፡**

**የጣት ጥፍር እንክብካቤ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ እና ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| ጎድጓዳ ሳህን ውስጥ ውሃ ያድርጉ፡፡  ውሃው ደህንነቱ የተጠበቀ እና ለደንበኛው ምቹ በሆነ የሙቀት መጠን ላይ መሆኑን ያረጋግጡ፡፡  አስፈላጊ ከሆነ ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| ለደንበኛው ውሃ በሚመች ደረጃ ላይ ያስቀምጡ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን ጣቶች በውሃ ውስጥ ያጥልቁ እና እንዲፈገፍገው ይፍቀዱ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን የጣት ጥፍሮች ከመሞረድዎ ወይም ከማፅዳትዎ በፊት፣ በጣቶች መካከል ጨምሮ የደንበኛውን እጅ ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን እጅ በማሸት ሳይሆን ቸብቸብ በማድረግ ድርቁት | ☐ | ☐ |
| በቢጫው ስንጥር ጥፍር ስር ያፅዱ፡፡ እያንዳንዱን ጥፍር ካፀዱ በኋላ ቢጫውን ስንጥር በፎጣው ላይ ይጥረጉት | ☐ | ☐ |
| የብርጭቆ ወረቀት መሰል መሞረድ ጥፍሩን ለስላሳ እና የማይዋጋ  በማድረግ ይጨርሱ | ☐ | ☐ |
| መሞረጃውን ወደ ፊት እና ወደ ኋላ በማንቀሳቀስ ያለስልሱ ግን ጥፍር እንዲሰነጠቅ እና እንዲ ሳሳ ሊያደርግ ስለሚችል በጠርዞቹ በኩል ወደ ውስጥ እንዳት ገቡ | ☐ | ☐ |
| ጥፍርን በአንድ አቅጣጫ ከአንድ ወገን ወደ ሌለው ጎን ይሞርዱት ወይም እያንዳንዱን ጥፍር አናት ከአንድ ጥግ ወደ መካከል  ይሞርዱት | ☐ | ☐ |

**የጣት ጥፍር እንክብካቤ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| በጥፍር ስር ያሌ የሞቱ ትሹዎች ለእንፌክሽን እንደ መከላከያ ያገዳል፡፡ የሞቱ ትሹዎችን አታውጡ | ☐ | ☐ |
| ጥፍሮችን በማለስለስ እና ሹካራ ጫፎችን በማፅዳት ይጨርሱት | ☐ | ☐ |
| ሎሽን ለመቀባት ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| ባዶ የንፁህ ውሃ ጎድጓዳ ሳህን(ኖች)፣ የማስቀመጫ እቃዎች፣ በጥቅም ላይ የዋሎ ሊኖ(ዎች)ን መጣል እና በትክክል ይጣሉ እና ሁደቱ ሲያጠናቅቁ ጠረጴዛውን በማድረቅ ይተውት | ☐ | ☐ |
| ጓንት ያውልቁ እና እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ደንበኛው የሚመላለስ ችግር ወይም የስኳር በሽታ ካለው፣ የቤት እንክብካቤ እርዳታ በደንበኛው**
**የጣት ጥፍሮች ላይ ቢጫውን ስንጥር አይጠቀምም፡፡**

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው ጠረጴዛ አጠገብ ይቀመጣል፡፡**

**የእግር እንክብካቤ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ እና ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በጣቶቹ መካከል እና የእግር ተረከዝን በመፈተሽ የአሰራር ሂደቱን ከመጀመርዎ በፊት የደንበኛውን እግር በጥንቃቄ ይመርምሩ፡፡ ከመጀመሩ በፊት ደንበኛው ህመም ወይም ስሱ የሆኑ አካባቢዎች እንዳሉት ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| ገንዳው ውስጥ ውሃ ያድርጉ ፣ ከግማሽ ያላነሰ ይሙሉት | ☐ | ☐ |
| እግር ሙሉ በሙሉ ከመግባቱ በፊት የውሃ ሙቀት ምቹ መሆኑን ደንበኛውን ይጠይቁ። አስፈላጊ ከሆነ ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን እግር ሙሉ በሙሉ በውሃ ውስጥ ያድርጉት | ☐ | ☐ |
| በሂደቱ ሁሉ ላይ እግር እና ቁርጭምጭሚትን በትክክል መደገፍ፣ እግርን ከውኃ ውስጥ ያስወግዱ ፣ የጣቶች መካከልን ጨምሮ መላውን እግር ሳሙና በነካው ማጠቢያ ጨርቅ ይጠቡ፡፡ **ለማለቅለቅያ ሳሙና የሌለው ውህ በገንዳ ያስቀምጡ፡ (1) በውኃ ገንዳ ውስጥ ሳሙና ከመጨመር ይልቅ ማጠቢያ ጨርቁን ሳሙና በማስነካት በማጠቢያ ጨርቅ እግርን ማጠብ፣ (2) ሁለት የተለያዩ የውሃ ገንዳዎችን በመጠቀም፡ አንዱ ለመታጠብ እና ሌላውን ለማለቅለቅ ይጠቀሙ** | ☐ | ☐ |
| ቀጥታ በውኃ ውስጥ ሳይሆን ሳሙናውን በእርጥብ ማጠቢያ ጨርቅ መጨመርዎን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| በየደንበኛውን እግሮች ሳሙና ባለው የማጠቢያ ጨርቅ ካሹ በኋላ ጣቶች መሃልን ጨምሮ ሙ እግርን ይጠቡ.... | ☐ | ☐ |
| ከእግር እና ከጣቶች መካከል ሳሙና ለማውጣት ያለቅልቁት | ☐ | ☐ |
| ከደንበኛው ጥፍሮች ስር ቆሻሻን ከማፅዳትዎ በፊት ስንጥር ከመጠቀምዎ በፊት ጣቶች መሃልን ጨምሮ እግሮቻቸውን በቀስታ ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| ጥፍር ስርን በቢጫው ስንጥር ካጸዱ በኋላ ስንጥሩን ከእያንዳንዳ ማፅዳት በኋላ በፎጣው ላይ ያፅዱ | ☐ | ☐ |
| ለማሳመር በመሞረጃው ወይም የብርጭቆ ውረቱን ጥፍርን በቀጥታ አስተካክለው ይሞርዱ | ☐ | ☐ |
| መሞረጃው ወይም የብርጭቆ ወረቀቱን ወደ ፊት እና ወደ ኋላ ይንቀሳቀሱት፡ ነገር ግን ጥፍር እንዲሰነጠቅ እና እንዲሳሳ ሊያደርግ ስለሚችል በጠርዞቹ በኩል ወደ ውስጥ እንዳትገቡ | ☐ | ☐ |
| ጥፍርን አቅጣጫ ከእንድ ወገን ወደ ሌለው ወገን ብቻ ወይም እያንዳንዱን የጥፍር ጫፍ ከአንድ ጥግ ወደ መካከል ይሞርዱት | ☐ | ☐ |
| በጥፍር ስር ያሉ የሞቱ ሴሎች ለእንፌክሽን እንደ መከላከያ ያገዳል፡፡ የሞቱት ሴሎች አታስወግዱ | ☐ | ☐ |
| ጥፍሮችን በማለስለስ እና ሹካራ ጫፎችን በማፅዳት ይጨርሱት | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ሎሽን እንዲደረግለት እንደሚፈልግ ይጠይቁ። እንደዚያ ከሆነ ሎሽን እጅዎ ላይ ያድርጉ እና የደንበኛውን ሙሉ እግር ላይ ቅባት ያድርጉ፤ ሎሽን በእግሮቹ ጣቶች መካከል አለማድረግን ያረጋግጡ፡፡ ከመጠን በላይ ሎሽን (ካለ) በፎጣ ያስወግዱ | ☐ | ☐ |
| ካልሲዎችን እና ጫማዎችን እንዲቀይር ደንበኛን ይረዱ | ☐ | ☐ |
| የመታጠቢያ ገንዳውን ባዶ አድርገው ይጠቡ እና ወደ ተገቢው ማስቀመጫቻ ቦታ ይመለሱ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ያስወግዱ እና እጅዎን ይታጠ | ☐ | ☐ |

**ደንበኛው የሚመላለስ ችግር ወይም የስኳር በሽታ ካለው፣ የቤት እንክብካቤ እርዳታ በደንበኛው**
**የጣት ጥፍሮች ላይ ቢጫውን ስንጥር አይጠቀምም፡፡**

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው በወንበር ላይ ይቀመጣል፡፡**

| ለደንበኛ ጥፍር እንክብካቤ ሲረዱ የሚከተሉት አጠቃላይ ምክሮች ናቸው፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የቀለም ለውጦች (በተለይም መቅላት) ፣ የሙቀት መጠን ፣ አረፋዎች ፣ መቆረጥ ወይም መቧጨር ፣ በእግር እና እጅ ጣቶች መካከል ያሉ ስንጥቆች ወይም ሌሎች ለውጦች በደንበኛዎ እግር እና እጅ ላይ መኖሩን በየጊዜው ይመርምሩ፡፡ በአከባቢው ዙሪያ የሚያዩትን ማናቸውንም እብጠት ወይም መቅላት ይመዝግቡ እና ያሳውቁ ፡፡ ሁል ጊዜም የደንበኛን የጥፍር እንክብካቤ ከማድረግዎ በፊት የደንበኛን እንክብካቤ እቅድ ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| ጥቃቅን መቆረጦችን ይከታተሉ እና ያፅዱአቸው | ☐ | ☐ |
| በጣቶች መካከል ሎሽን አይቀቡ - ሎሽኑ የፈንገስ እድገትን የሚያራባ እርጥበትን ያስከትላል | ☐ | ☐ |
| የደንበኛን ጥፍሮች ጥግ አይቁረጡ ወይም በጥፍሩ ዙሪያ ለማንኛውም ደንበኛ በሹል መሳሪያ አይቆፍሩ | ☐ | ☐ |
| ለስላሳ፣ ንፁሁ ጥፍሮች ምቾትን እና ሰላምን ለደንበኛ ሰጣሉ፡፡ ወጣ ገባ ወይም ሹል ጥፍር ልብን መያዝ እና መቅደድ እና ምናልባትም ለእግር/ እጅ ጣቶች ጉዳትን ማስከተል ይችል ይሆናል፡፡ ሁል ጊዜም የደንበኛን እግር እና እጅ በጥንቃቄ እና በቀስታ ያያዙ | ☐ | ☐ |

| የለመልበስ ደካማ የሆነ ክንድ ያለውን ደንበኛ መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኞች ምን መልበስ እንደሚፈልጉ ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| እጅ/እግር እና መገጣጠሚያዎች ላይ ሀይል መጠቀም እና መጎተትን በማስወገድ የደንበኛውን ሰውነት በቀስታ እና በተፈጥሮ በማንቀሳቀስ ሁሉንም ልብሶች ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው በሚሰራ ክንዱ ልብሱን ከማድረጉ በፊት በማይሰራው ክንድ ሸሚዝ ፣ ሹራብ ትክክለኛውን እጀታ ላይ እንዲያደርግ ይረዱ፡፡  በሚሰራው ክንድ ከማድረግዎ በፊት የሸሚዝ እጅጌን በደካማ ክንድ ላይ ያድርጉት | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው እንዲለብስ ይጠቁሙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው እግሮቹን በሱሪ ውስጥ ሲያስገባ እና የማያንሸራትት ጫማን እንዲለብስ በሚረዱነት ጊዜ መቀመጡን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| ሱሪ ሲጎትቱ እና ሲያደርጉ ለደንበኛው ድጋፍ ይስጡ | ☐ | ☐ |
| በደንበኛው በደንበኛ (በቀኝ በኩል ውጭ ልብስ ፣ ዚፐሮች / ቁልፎች ወ.ዘ.ተ) ለብሰው ሲቀመጡ ይጨርሱ | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎቶች ሙከራ ደንበኛው መቆም ይችላል፡፡ ደንበኛው ቲሸርት እና የውስጥ ሱሪ ለብሶ  ሸሚዝ ፣ ሱሪ፣ ካልሲ እና ጫማ መልበስ ያስፈልጋል፡፡ ደንበኛው በራሳቸው ልብስ ላይ ይለብሳሉ፡፡**

| ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ቢያንስ ተረከዝ ድረስ ከውስጥ ወደ ውጭ በማዞር ካልሲውን ለማድረግ ያዘጋጁ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን እግር በተፈጥሯዊ ማንቀሳቀስ፣ በአግባቡ የማይንቀሳቀሱትን መደገፍ እና የእጅ/ እግር እና መገጣጠሚያዎችን ከመጠን በላይ መጎተት እና ሀይልን በማስወገድ በእግር ጣቶች፣ በእግር እና ተረከዝ ላይ ካልሲውን ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በእግር፣ ተረከዝ እና እግር ላይ የካልሲውን አናት ይጎትቱ | ☐ | ☐ |
| ካሲው ለስላሳ፣ ያለ ምንም ጠመዝማዛ ወይም መጨማደድ፣ እና በደንበኛው ጣቶች ላይ በጣም ጥብቅ አለመሆኑን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| በካልሲው ዲዝይን መሰረት የእግር ጣት እና ተረከዝ በአግባቡ በማድረግ ካልሲ ማድረጉን ያጠናቅቁ | ☐ | ☐ |
| ካልሲው እስከ ጉልበት ሆኖ እና ከመጨማደድ ነፃ ሆኖ ይተውት | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ  ይህ እንክብካቤ  በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው አልጋ ላይ ይተኛል፡፡**

| የቀስታ እንቅስቃሴ  ለአንድ ትከሻ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ክህሎቶች | ☐ | ☐ |
| በሚከተሉት የሰውነት እንቅስቃዴዎች ውስጥ እጅ እና እግር በሚረዳበት ወቅት፣ በጋር በርጋታ፣ በቀስታ፣  እና ለስለስ በማድረግ በእንቅስቃሴዎች በሙሉ እስከሚያስቸግርበት ቦታ ድረስ ያንቀሳቅሱ፡፡ ህመም ከተሰማ ያቁሙት | ☐ | ☐ |
| በእንቅስቃሴዎች በሙሉ ደንበኛውን የምቾታቸውን ደረጃ ይጠይቁ ህመም ከተሰማ ያቁሙት | ☐ | ☐ |
| ለትከሻ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በሚሰራበት ወቅት፣ የደንበኛውን ወገብ እና ክንድ ስር በመያዝ ይደግፉ | ☐ | ☐ |

**የቀስታ እንቅስቃሴ ለአንድ ትከሻ - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ (የቀጠለ)፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የተስተካከለውን የደንበኛ ክንድ ወደ ጣሪያ ያንሱ፣ ወደ አልጋ ራስጌ (HOB) እንደገና ይመለሱ እና ከዚያም ወደ ጠፍጣፋ ቦታ ይመለሱ፤ ይህ አንድ ድግግሞሽ (የትከሻ መታጠፍ / ማራዘሚያ) ነው። ቢያንስ ሦስት (3) ጊዜ ይድገሙት | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን የተስተካከለ ክንድ ከሰውነቱ ጎን በማንሳት ወደ HOB ያንቀሳቅሱ እና የደንበኛውን የተስተካከለ ክንድ ወደ የደንበኛው አካል ይመልሱ፤ ይህ አንድ ድግግሞሽ (የትከሻ መያዝ / መጨመሪያ) ነው። ቢያንስ ሦስት (3) ጊዜ ይድገሙት | ☐ | ☐ |
| በደንበኛው የትከሻ ደረጃ የደንበኛን ተጣጣፊ ክርን ያስቀምጡ፣ ክንድ ወደ HOB ያዙሩ እና ክንድዎን ወደ ታች ወደ ዳሌ ያዙሩ። ቢያንስ ሦስት (3) ጊዜ ይድገሙት | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ ይህ እንክብካቤ በሚሲሰጥበት ወቅት ደንበኛው አልጋ ላይ ይተኛል፡፡**

**የቀስታ እንቅስቃሴ ለአንድ ጉልበት እና ቁርጭምጭሚት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| በሚቀጥሉት እንቅስቃሴዎች እጅ/እግርን ሲደግፉ ፣ መገጣጠሚያውን በእርጋታ ፣ በቀስታ እና በተቀላጠፈ የእንቅስቃሴው ክልል ውስጥ እስከሚገደቡ ድረስ ያንቀሳቅሱ | ☐ | ☐ |
| **ቁርጭምጭምት፡** የጉልበት እንቅስቃሴን በሚያከናውንበት ጊዜ የደንበኛውን እግር በጉልበት እና በቁርጭምጭሚት መገጣጠሚያዎች ላይ ይደግፉ | ☐ | ☐ |
| በአካል ብቃት እንቅስቃሴው ወቅት ደንበኛው ምን እንደሚሰማው ይጠይቁ ፡፡ ህመም ከተከሰተ ያቁሙ | ☐ | ☐ |
| ጉልበቱን እስከማይችሉ ድረስይጠፉ እና ከዚያ እግርን ወደ አልጋው ይመልሱ (ጉልበትን ቀጥ ማድረግ እንደ አንድ ድግግሞሽ - የጉልበት መታጠፍ / ማራዘሚያ)። ቢያንስ ሦስት (3) ጊዜ ይድገሙ | ☐ | ☐ |
| **ቁርጭምጭምት፡** ለቁርጭምጭምት እንቅስቃሴን በሚያከናውንበት ጊዜ እግርን እና ቁርጭምጭምትን ይደግፉ | ☐ | ☐ |
| ያችኛውን እግር ወደ እግሩ ወደፊት ይግፉት፣ እና በተለየ እንቅስቃሴ እግሩን ወደ ታች ወደ አልጋው ግርጌ ይግፉት እንደ አንድ ድግግሞሽ (የቁርጭምጭሚት ማጠፍ / ማራዘሚያ)፡፡ ሦስት (3) ጊዜ ይድገሙት | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው አልጋ ላይ ይተኛል፡፡**

**ደንበኛ እንዲበላ መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| **እርዳታ ከመጀመሩ በፊት ደንበኛው ወንበር ላይ ቀጥ ብሎ መቀመጡን ያረጋግጡ** | ☐ | ☐ |
| ለደንበኛ የልብስ መከላከያ ያቅርቡ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው እንዲበላ ለመርዳት በደንበኛው ዐይን ደረጃ ልክ ይቀመጡ | ☐ | ☐ |
| የቀረቡ የምግብ ዓይነቶችን በማቀያየር ወይም ለእያንዳንዱ ጉርሻ የደንበኛውን ምርጫ በመጠየቅ በአንድ ጉርሻ መጠን በመቆራረጥ ምግብ ያቅርቡ | ☐ | ☐ |
| በምግብ ወቅት ለደንበኛው መጠጥ ያቅርቡ | ☐ | ☐ |
| የሚቀጥለውን ጉርሻ ወይም መጠጥ ከመስጠትዎ በፊት የደንበኛው አፍ ባዶ መሆኑን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| ምግብ በሚመገቡበት ጊዜ ሁሉ ደንበኛን በውይይት ውስጥ ያሳትፉ | ☐ | ☐ |
| ምግብን ከደንበኛው አፍ እና እጅ እንደ አስፈላጊነቱ እና በምግብ መጨረሻ ላይ ይጥረጉ | ☐ | ☐ |
| ከተለበሰ የልብስ መከላከያውን ያስወግዱ እና በተገቢው መያዣ ውስጥ ይጣሉት | ☐ | ☐ |
| የተረፈውን ምግብ ያስወግዱ | ☐ | ☐ |
| ጠረጴዛውን ንፁህ ፣ ደረቅ እና ከምግብ ዕቃዎች ያፅዱ | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ ለዚህ እንክብካቤ በሚጀምር ወቅት ደንበኛው ጠረጴዛ አጠገብ ይቀመጣል፡፡**

**ደንበኛው በገንዳ ሰውነት መታጠብን መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡**

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የላይኛውን አልጋ ያስወግዱ ወይም ይጥፉት፡፡ ደንበኛው በመታጠቢያ ብርድ ልብስ ወይም በላይኛው አንሶላ እንዲሸፈን ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የደንበኞችን ጋዎን / የእንቅልፍ ልብሶችን ያስወግዱ | ☐ | ☐ |
| የውሃው ሙቀት ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ እና ለደንበኛው ምቹ በሆነ የሙቀት መጠን መሆኑን ያረጋግጡ አስፈላጊ ከሆነ ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |

| ደንበኛ በገንዳ ሰውነት መታጠብ መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ (የቀጠለ)፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| ሳሙና የሌለው ውሃ ለማለቅለቅ በገንዳ ያስቀምጡ፡፡ (1) በውኃ ገንዳ ውስጥ ሳሙናን በቀጥታ ከመጨመር ይልቅ ማጠቢያ ጨርቁን ሳሙና በማስነካት በማጠቢያ ጨርቅ ማጠብ፤ (2) ሁለት የተለያዩ የውሃ ገንዳዎችን በመጠቀም፡ አንዱ ለመታጠብ እና አንዱ ለማለቅለቅ ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ውሃ አረፋ ከሆነ፣ ከቀዘቀዘ ወይም ከቆሸሸ በማንኛውም ጊዜ ይተኩ | ☐ | ☐ |
| ከደንበኛው ራስ / አንገት በስተጀርባ ደረቅ ፎጣ ያስቀምጡ | ☐ | ☐ |
| እርጥብ ማጠቢያ ጨርቅ (ሳሙና የሌለው) በመያዝ ከአይን ይጀምሩ፡፡ ለእያንዳንዱ ዐይን ከውስጥ እስከ ውጭ ጥግ በማጠብ የማጠቢያውን ልብስ የተለያየ ቦታ ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ቀሪውን ፊት፣ ጆሮ እና አንገት ሳሙና በመጠቀም ይጠቡ (ደንበኛው የሚመርጥ ከሆነ) | ☐ | ☐ |
| ያለቅልቁ እና አካባቢን በፎጣ ያድርቁ - በቀስታ፣ አይፈትጉ | ☐ | ☐ |
| አንድ ክንድ ያንሱ እና ከእሱ በታች አንድ ፎጣ ያስቀምጡ፡፡ የደንበኛውን ክንድ ከክርን በታች በእጅዎ መዳፍ ይደግፉ። የደንበኛውን ክንድ ፣ ትከሻ እና ብብት ማጠብ፡፡ አለቅልቀው ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን እጅ በውኃ ገንዳ ውስጥ ያኑሩ። የደንበኛውን እጅ ይጠቡ ፣ ያለቅልቁ እና ያድርቁ፡፡ በሌላኛው ክንድ እና እጅ ይድገሙ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን ደረትን እና ሆዱን ይጠቡ ፣ ያለቅልቁ እና ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| ከደንበኛው እግር አንዱን ይግለጡ እና ከታችኛው እግር እና ከእግር በታች ረዥም ፎጣ ያድርጉ፡፡ ጉልበቱን ይጠፉ እና እግርን በክንድዎ ይደግፉ፡፡ እግሩን ይጠቡ ፣ ያለቅልቁ እና ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛውን እግር በውኃ ገንዳ ውስጥ በማንሸራተት ይጨምሩ፡፡ የደንበኛውን የታችኛው እግር ይጠቡ ፣ ያለቅልቁ እና ያድርቁ፡፡ በሌላኛው ይድገሙ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ከእርስዎ በመራቅ በጎናቸው እንዲዞር ይርዱት። የመታጠቢያ ብርድ ልብስ ወይም ፎጣ ከጀርባዎቻቸው ጋር ያድርጉ | | |
| የደንበኛውን ጀርባ እና መቀመጫ ያለቅልቁ እና ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን ከጀርባው ይርዱት፡፡ ግላዊነትን በመጠበቅ ደንበኛው የራሳቸውን የብልት እንክብካቤ እንዲያከናውን ያድርጉ (ከተቻለ)፣ ካልሆነ ይህ ተግባር በተናጠል ተሸፍኗል | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን ይተውት | ☐ | ☐ |
| በእንክብካቤው መጨረሻ ደንበኛውን በላይኛው አንሶላ እና/ወይም አልጋው ይሸፍኑት | ☐ | ☐ |
| እርጥብ ሊሆን የሚችል የአልጋ ልብሶችን ያስወግዱ | ☐ | ☐ |
| የቆሸሸ ልብሶችን እና ጨርቆችን በተገቢው መያዣ ውስጥ ያስቀምጡ | ☐ | ☐ |
| የመታጠቢያ ገንዳዎችን ባዶ በማድረግ ፣ ማጠብ ፣ ማፅዳት ፣ ከተዋህሲያን ነጻ ማድረግ እና ወደ ተገቢ ማስቀመጪያ መመለስ | ☐ | ☐ |
| የቆሸሹ ጓንቶችን ያውልቁ እና ያስወግዱ፣ እጅዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

| የብልት እንክብካቤ መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡ | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ገንዳውን በውሃ ይሙሉ ፣ ለደንበኛው ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ የሙቀት መጠን ያለው ውሃ ይጠቀሙ ፡፡ እንደተጠየቀው ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| የብልት እንክብካቤ በሚሰጥበት ጊዜ ፣ መሣሪያዎችን በማጠብ እና በማድረቅ እንዲሁም የቆሸሹ ልብሶችን በሚይዙበት ጊዜ ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የደንበኛን አልጋ በፎጣ ወይም በሚጣል የአልጋ ንጣፍ እርጥብ እንዳይሆን ይጠብቁ | ☐ | ☐ |
| የብልቱን አካባቢ ይግለጡ፡፡ የደንበኛው ግላዊነት የተጠበቀ መሆኑን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| ሳሙና የሌለው ውሃ ለማለቅለቅ በገንዳ ያስቀምጡ፡፡ (1) በውኃ ገንዳ ውስጥ ሳሙና ከመጨመር ይልቅ ማጠቢያ ጨርቁን ሳሙና በማስነካት በማጠቢያ ጨርቅ ማጠብ፤ (2) ሁለት የተለያዩ የውሃ ገንዳዎችን በመጠቀም፡ አንዱ ለመታጠብ እና አንዱ ለማለቅለቅ | ☐ | ☐ |
| ሙሉውን የብልት ክፍል በቀስታ በሳሙና ማጠቢያ ጨርቅ ይጠቡ፡፡ ለመጥረግ የመታጠቢያ ጨርቅ ንፁህ ቦታ ይጠቀሙ፡፡ የብልቱን አካባቢ ከፊት እስከ ጀርባ ያፅዱ | ☐ | ☐ |
| ሙሉውን የብልት ክፍል በንጹህ ማጠቢያ ጨርቅ ያጠቡ፡፡ ለእያንዳንዱ መጥረግ ንጹህውን የማጠቢያ ጨርቀተ ቦታ ይጠቀሙ፡፡ የብልቱን አካባቢን ከፊት ወደኋላ ያለቅልቁ | ☐ | ☐ |
| ከፊት ወደ ኋላ በመንቀሳቀስ የብልቱን አካባቢን በቀስታ ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| **ወደ ጎን ለማዞር ደንበኛን ይረዱ፡፡ ደንበኛው ከአልጋው ጫፍ ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት መሆኑን ያረጋግጡ** | ☐ | ☐ |
| የቂጥ እና ፊንጢጣን አካባቢን ይጠቡ ፣ ያለቅልቁ እና ያድርቁ፡፡ ለእያንዳንዱ መጥረግ ንጹህ የማጠቢያ ቦታን ይጠቀሙ፡፡ የብልት አካባቢን እንዳይበከል ለመከላከል ከፊት ወደ ኋላ ይጥረጉ | ☐ | ☐ |
| አስፈላጊ ከሆነ የአልጋ ንጣፍ ወይም የታችኛው አንሶላ ይቀይሩ | ☐ | ☐ |
| በሂደቱ ወቅት የደንበኞቹን ሰውነት መጋለጥ ይቀንሱ | ☐ | ☐ |
| በእንክብካቤው መጨረሻ ደንበኛውን ከላይ በአንሶላ እና/ ወይም በብርድ ልብስ ይሸፍኑ | ☐ | ☐ |
| የቆሸሹ ወይም እርጥብ ማጠቢያ ልብሶችን ፣ ፎጣዎችን ፣ የአልጋ ንጣፎችን ፣ የአልጋ ልብሶችን ወይም ልብሶችን ያስወግዱ ፡፡ በተገቢው መያዣዎች ውስጥ ይጣሉ | ☐ | ☐ |
| የቆሸሹ ጓንቶችን ያውልቁ እና ያስወግዱ | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎቶች ሙከራ ደንበኛው ሴት አሻንጉሊት ነው፡፡ ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ጊዜ ደንበኛው አልጋው ላይ ተኝቷል፡፡**
**ይህ ክህሎት የሚከናወነው ሳሙና እና ውሃ በመጠቀም እንጂ መጥረጊያ በመጠቀም አይደለም፡፡**

## የብልት እንክብካቤ መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች | ☐ | ☐ |
| ገንዳውን ውስጥ ውሃ ይመልከቱ:: ፣ ለደንበኛው ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ የሙቀት መጠን ያለው ውሃ መሆኑን ይወስኑ:: እንደ ተጠየቀው ያስተካክሉ | ☐ | ☐ |
| ሳሙና የሌለው ውሃ ለማለቅለቅ በገንዳ ያስቀምጡ:: (1) በውኃ ገንዳ ውስጥ ሳሙና ከመጨመር ይልቅ ማጠቢያ ጨርቁን ሳሙና በማስነካት በማጠቢያ ጨርቅ ማጠብ፣ (2) ሁለት የተለያዩ የውሃ ገንዳዎችን በመጠቀም፡ አንዱ ለመታጠብ እና አንዱ ለማለቅለቅ | ☐ | ☐ |
| በእንክብካቤ ወቅት የደንበኛ ሰውነት መጋለጥን ይቀንሱ | ☐ | ☐ |
| የብልት አካባቢን ከመንካት በፊት፣ ቱቦን ከማስገባት እና ማውጣት፣ የሽን መያዣ ከረጢትን ከመንካት በፊት ወይም ማፅዳት ከመጀመር ወይም በአጠቃላይ ለብልት አካባቢ እንክብካቤ በመስጠት ሂደት ውስጥ፣ እቃዎችን በማድረቅ እና በማፅዳት እንዲሁም የቆሸሹ ልብሶችን ስነካ የእጅ ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| **ደንበኛውን በእንክብካቤ ወቅት በጎን ከሆኑ፣ ከአልጋው ጫፍ ደህንነቱ የተጠበቀ ርቀት መሆኑን ያረጋግጡ** | ☐ | ☐ |
| ከማጠብዎ በፊት የደንበኛው አንሶላዎች ወይም ልብሶች በፅዳት ወቅት እንዳይረጥቡ. ከሽንት መቀበያው ቱቦ ስር ፎጣ ወይም ፓድ ያስቀምጡ | ☐ | ☐ |
| የብልት አካባቢ ብቻን ይግለጡ | ☐ | ☐ |
| ሙሉውን የብልት ክፍል በቀስታ በሳሙናማ ማጠቢያ ጨርቅ ይጠቡ | ☐ | ☐ |
| ለእያንዳንዱ መጥረግ እና ማጠብ ንጹህ የማጠቢያ ጨርቁን ቦታን በማዘዋወር ይጠቀሙ:: የሽንት ቱቦውን አይመንጭቁት:: እንዳይወጣ ለመከላከል ቱቦው ወደ ሰውነት የገባበት አካባቢ ይያዙ | ☐ | ☐ |
| ቢያንስ ከታቴተሩን መግቢያ አካባቢ አራት እንች ያፅዱ፣ ከገላ ወደ ታች ወደ ሚፈስበት ይሂዱ:: ለእያንዳንዱ ፅዳት ንፁህ የማጠቢያ ጨርቅን ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| የተለያዩ የማጠቢያ ጨርቅን መጠቀም፣ ከታቴተሩን መግቢያ አካባቢ አራት እንች ያፅዱ፣ ከገላ ወደ ታች ወደ ሚፈስበት ይሂዱ:: ለእያንዳንዱ ፅዳት ንፁህ የማጠቢያ ጨርቅን መጠቀም | ☐ | ☐ |
| የትኛውንም የደንበኛን የራሰ ቆዳን አከባቢ ማድረቅ | ☐ | ☐ |
| በእንክብካቤ ወቅት የራሰ ቆዳን አካባቢ ይተው እና በእንክብካቤው መጨረሻ አንሶላዎችን ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| በእንክብካቤ ወቅት በሙሉ እና በሂደቱ መጨረሻ የሽንት መቀበያ ላስቲኩን ከኩላሊት ትይዩ በታች ያስቀምጡ:: በካቴተሩ ምንም እጥፋት አለመኖሩን ማረጋገጥ አለብዎት | ☐ | ☐ |
| ፎጣዎችን እና ሌሎች ነገሮችን በተገቢው ማስቀመጫ ያኑሩ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን በእንክብካቤው መጨረሻ ከላይ ሽፍነው ይተውት | ☐ | ☐ |
| የእጅ ጓንትን አውልቀው ይጣሉት እና እጅ ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎቶች ሙከራ ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው አልጋው ላይ ተኝቷል::**

## የኮንዶም ካቴተር እንክብካቤ

| | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የብልት አካባቢን ብቻ ይግለጡ | ☐ | ☐ |
| ብልትን በጥንቃቄ ይጠቡ እና ያደርቁ ፣ ረዥም ፀጉሮችን ይቁረጡ | ☐ | ☐ |
| የተሰነጠቀ ቦታ እንዳለ ለማየት የወንዶች ብልትን ቆዳ ያስተውሉ | ☐ | ☐ |
| ቁስሎች ወይም የተሰነጠቀ ቦታዎች ካሉ ፣ ኮንዶምን አይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| በወንድ ብልት ላይ የቆዳ ማጣበቂያ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በወንድ ብልት ላይ የኮንዶም ካቴተር ያስገቡ | ☐ | ☐ |
| ኮንዶምን ከቧንቧ ጋር ያያይዙ:: የኮንዶሙ ጫፍ እንዳልተጣመመ ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| ቧንቧውን ከደንበኛው እግር ጋር ያያይዙ። ማጠራቀሚያ ላስቲኩ ከፊኛው በታች መሆኑን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| ጓንትዎችን ያውልቁ እና ያስወግዱ እና እጅዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

| **የመድሀኒት እገዛ - ይህንን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋል፡** | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| የደንበኞችን የመድኃኒት መርሃግብር ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| የታዘዘላቸውን መድሃኒት የሚወስድበት ጊዜ መሆኑን ለደንበኛው ያስታውሱ | ☐ | ☐ |
| **በደንበኛው ስም የተሰየመ ትክክለኛውን የመድኃኒት ጠርሙስ ይምረጡ** | ☐ | ☐ |
| የመድኃኒት መያዣውን ከተቀመጠበት ቦታ ይውሰዱት ፣ መለያውን ይመልከቱ እና 5 መብቶችን ያረጋግጡ - መድሃኒት ፣ ደንበኛ ፣ መጠን ፣ አወሳሰድ እና ጊዜ | ☐ | ☐ |
| መያዣውን ይክፈቱ ፣ መለያውን ይመልከቱ እና 5 መብቶቹን እንደገና ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| መድሃኒቱን ሳይነኩ ከጠርሙሱ ወደ ክዳኑ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| መድሃኒቱን ሳይነኩ ከክዳኑ ወደ እጃቸው በማፍሰስ ለደንበኛው ትክክለኛውን የክኒን ብዛት ይስጡት | ☐ | ☐ |
| ደንበኛን መድሃኒት እንዲወስድ ያመቻቹ | ☐ | ☐ |
| **እጅዎ በደንበኛው እጅ ላይ ሳያርፍ ወይም ክኒን(ዎችን) በደንበኛው አፍ ላይ ለማስገባት የደንበኛው እጅ ሳይነካ ወይም ኪኒንውን በቀጥታ በደንበኛው አፍ ውስጥ ሳያደርጉ ደንበኛው መድሃኒት እንዲወስድ ይረዱታል** | ☐ | ☐ |
| ለደንበኛው (በአፍ መድሃኒቶች) ለመውሰድ አንድ ሙሉ ብርጭቆ ፈሳሽ ያቅርቡ | ☐ | ☐ |
| መድሃኒቱ መወሰዱን ልብ ይመልከቱ እና ያረጋግጡ፡፡ መድሃኒቱን መዋጡን ደንበኛውን ይጠይቁ ወይም ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| የመድኃኒት መያዣውን ይዝጉት እና በተገቢው ቦታ መልሰው ያስቀምጡት፣ እንደገና አምስት (5) መብቶችን ያረጋግጡ፡፡ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው መድሃኒቱን እንደወሰደ ይመዝግቡ። ካልወሰዱም፤ ያንንም ይመዝግቡ | ☐ | ☐ |
| እጅን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

**ለ HCA ክህሎት ሙከራ ይህ እንክብካቤ በሚሰጥበት ወቅት ደንበኛው ጠረጴዛ አጠገብ ይቀመጣል፡፡**

| **ደንበኛ የአልጋ ላይ ፖፖ መጠቀም መርዳት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡** | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| የ S.W.I.P.E.S. የግንኙነቶች / የደንበኞች መብቶች እና የተለመዱ የእንክብካቤ ልምዶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| የአልጋ ላይ ፖፖ ከማስቀመጥዎ በፊት የአልጋውን ራስጌ ዝቅ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| በደንበኛው መቀመጫዎች ስር የአልጋ ላይ ፖፖ በትክክል ለማስቀመጥ ጓንት ያድርጉ (መደበኛ የአልጋ ላይ ፖፖ: የፖፖው ሰፊው ጫፍ ከደንበኛው መቀመጫ ጋር የተስተካከለ እንዲሆን አድርገው ያስገቡ፣ ግማሽ ፖፖ: የፖፖውን መያዣ ወደአልጋው ግርጌ በማድረግ ያስገቡ)። ደንበኛው ጉልበቶቹን እንዲያጥፍ እና ዳሌውን ከፍ እንዲያደርግ ያድርጉ (ከተቻለ) | ☐ | ☐ |
| በደንበኛው ስር የአልጋ ላይ ፖፖ ካስገቡ በኋላ የአልጋውን ራስጌ ከፍ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የመፀዳጃ ሶፍት በደንበኛው ተደራሽነት ውስጥ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| ሲጠናቀቁ ደንበኛው እንዲያሳውቅዎት ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛውን አንሶላ ወይም ብርድልብስ ለማልበስ ይጠይቁ | ☐ | ☐ |
| የአልጋ ላይ ፖፖ ከማስወገድዎ በፊት የአልጋውን ራስጌ ዝቅ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የአልጋ ላይ ፖፖ ከማስወገድዎ በፊት ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| የአልጋ ላይ ፖፖ ያንሱ እና ቆሻሻውን ወደ መጸዳጃ ቤት ያስወግዱ | ☐ | ☐ |
| የብልት እንክብካቤ ይስጡ (የቅደም-ተከተል ዝርዝር ይከተሉ) | ☐ | ☐ |
| መሣሪያዎችን በፕሮቶኮል መሠረት ማጽዳትና ከተዋህሲያን ነጻ ማድረግ፡፡ ወደ ትክክለኛው ማስቀመጫ ይመለሱ | ☐ | ☐ |
| ጓንትዎችን ያውልቁ እና ያስወግዱ እና እጅዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

| **በደህንነት ምላጭ መላጨት - ይህን ክህሎት በተሳካ ሁኔታ ለማሳየት የሚከተሉት ያስፈልጋሉ፡** | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|
| S.W.I.P.E.S. ክህሎቶች ይጠቀሙ | ☐ | ☐ |
| ጓንት ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| ደንበኛው ሰው-ሰራሽ ጥርስ እንደሚጠቀም ይጠይቁ፡፡ እንደዚያ ከሆነ በአፋቸው ውስጥ መሆናቸውን ያረጋግጡ | ☐ | ☐ |
| ፊትን በሙቅ እርጥብ ማጠቢያ ጨርቅ ይጠቡ | ☐ | ☐ |
| የሚላጨው አካባቢ የመላጫያ አረፋ ያድርጉ | ☐ | ☐ |
| ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ምላጭ ይያዙ | ☐ | ☐ |
| ቆዳ ወጥረው በነፃ እጅ ይያዙ እና በፀጉር በአቅጣጫ ለስላሳ እንቅስቃሴዎች ይላጩ | ☐ | ☐ |
| ምላጩን ንፁህ እና እርጥበታማ ለማድረግ አንዴ በላጩ ቁጥር በሞቀ ውሃ ውስጥ የደህንነት ምላጭ ያለቅልቁ | ☐ | ☐ |
| በመጀመሪያ ጎኖቹን ይላጩ ፣ ከዚያ አፍንጫ እና አፍ ይላጩ | ☐ | ☐ |
| ፊት አጥበው ፣ አለቅልቀው ያድርቁ | ☐ | ☐ |
| መሣሪያዎችን ማጽዳትና ማስቀመጥ | ☐ | ☐ |
| ጓንትዎችን ያውልቁ እና ያስወግዱ እና እጅዎን ይታጠቡ | ☐ | ☐ |

ለቤት እንክብካቤ ረዳቶች የክህሎት ልምምዶች አሠራር ማረጋገጫ ዝርዝር
በ DSHS የጸደቀ

# የ HCA በስራ ላይ የክህሎቶች ልምምድ ስልጠና ማጠናቀቅያ ማረጋገጥ
# በተቋሙ መምህራን በ AFH፣ ALF፣ ወይም በ ESF ውስጥ የተሰጠ

**Skills Practice Procedure Checklist for Home Care Aides**
**DSHS Approved**

**Verification of HCS On The Job Skills Practice Training**
**Provided by Facility Instructor(s) in an AFH, ALF, or ESF**

**ይህ ገጽ በእያንዳንደ ተቋምዎ ላይ የሥራ -ላይ-ሙያዊ ሥልጠና ላጠናቀቀው *እያንዳንዱ* የቤት እንክብካቤ ረዳት እጩ ተወዳዳሪ ለ DSHS የሥልጠና ክፍል መላክ *አለበት*፡፡**

***ይህንን ገፅ ብቻ*** ለTrainingApprovalITPA@dshs.wa.gov በኢሜይል ይላኩ፤ ርዕሱን "Facility On-The-Job Training በማለት ያስገቡ፡፡

________________________________ ከደንበኛ ጋር በውስጥ በመስራት በተሳካ ሁኔታ በማሳየት፤ በአሁኑ በጸደቀው የDSHS ተቋም
የተማሪው ስም
መምህራን፣ በዚህ የአሠራር ዝርዝር ውስጥ የተካተቱት ለግል እንክብካቤ ተግባራት አስፈላጊ የሆኑ ሁሉም አስፈላጊ እርምጃዎች በሙሉ በዚህ ዝርዝር ሂደቶች ውስጥ ተካቷል፡፡

| የተቋሙ ስም | | የተቋሙ ሥልጠና ቁጥር<br>WA |
|---|---|---|
| የአስተማሪ ፊርማ | አስተማሪ ስም | የአስተማሪ የሥልጠና ኮድ ቁጥር |
| የተማሪዎች ፊርማ | የተማሪ ስም | የማጠናቀቂያ ቀን |

እባክዎን ያስተውሉ: ሁሉም የክፍሎት ተግባራት በተፈቀደ የተቋም አስተማሪ መማር እና በቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት ሠራተኛ / ተቀጣሪ ማሳየት አለባቸው፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፣ ደንበኛው ከሌለ ወይም ደንበኛው በተወሰነ የክህሎት ስልጠና ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ የማይስማማ ከሆነ የቤት እንክብካቤ ረዳት ክህሎቶች አፈፃፀም አሻንጉሊት ወይም የሥልጠና አጋርን በመጠቀም ሊገመገም ይችላል፡፡

**ይህንን ገጽ መሙላት አያስፈልግም እና የቤት ውስጥ እንክብካቤ ረዳት ሰራተኛው የሙያ ስልጠናውን በ DSHS በተቀጠሩ የማህበረሰብ መምህራን በክህሎት ላቦራቶሪ ውስጥ የተሰጠ ከሆነ ለ DSHS መልሰው ይላኩ፡፡**